

# “ከኛ ጋር ሳይሆን ሊፋለሟቸው ከመጡት አካላት ጋር ብቻ የሚዋጉ መሰሉን ነበር።”

በባህር ዳር ከተማ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወታደሮች ከህግ አግባብ ውጪ የተፈፀሙ ግድያዎች

ሰ


የጥናት ሪፖርት

# ማውጫ

**ዋና ዋና ማጠቃለያ** ........ **4**
ማጠቃለያዎች እና ምክረ ሃሳቦች ........ **6**

በኢትዮጵያ አማራ ክልል በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እና በፋኖ ታጣቂዎች መካከል እየተደረገ ባለው የትጥቅ ግጭት፣ የመከላከያ ሰራዊቱ ወታደሮች በባህር ዳር ከተማ ስድስት ሰላማዊ ሰዎችን ከህግ አግባብ ውጪ ገድለዋል። በዚህ አጭር ምርመራ ሪፖርት አምነስቲ ኢንተርንሽናል የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት እንዲያቆም እንዲሁም መንግስት አፋጣኝ ምርመራ እንዲያደርግ እና ወንጀለኞችን ለፍርድ እንዲያቀርብ አሳስቧል።

# ዋና ማጠቃለያ




*ባህር ዳር ከተማ እና ግጭት እንደተካሄደባቸው የተዘገበባቸው ወይም ግጭት እንዳስተናገዱ በሳተላይት ምስሎች እና ለማንም ሰው ተደራሽ ከሆኑ ምንጮች (open source) በማስረጃ የተረጋገጠባቸው አካባቢዎችን የሚያሳይ ካርታ። © አምነስቲ ኢንተርናሽናል*

በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም. በአማራ ክልል በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እና በፋኖ ሚሊሻ መካከል የትጥቅ ግጭት ተቀሰቀሰ። እነዚህ ተዋጊ አካላት በትግራይ ክልል ተከሰቶ በነበረው ጦርነት አጋር የነበሩ ቢሆንም አሁን ግን ጠላት ሆነዋል። በህዳር ወር 2015 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት እና ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት) ገጭት ማቆም ስምምነት ከተፈራረሙ በኋላ በፌደራል መንግስት እና በአማራ ክልል ልዩ ፖሊስ መካከል ውጥረት ተፈጠረ። በሚያዝያ ወር 2015 ዓ.ም. የፌደራል መንግስት የክልል ልዩ ኃይሎችን ወደ ፌደራል የፀጥታ ሃይሎች መዋቅር ለማዋሃድ ውሳኔ ማሳለፉን ተከትሎ በውሳኔው ቅር የተሰኙ የአማራ ልዩ ፖሊስ ሃይል አባላት የፋኖ ሚሊሻን ተቀላቀሉ። ይህንንም ተከትሎ በፋኖ ታጣቂዎችና በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት መካከል ግጭት ተቀስቅሶ የፋኖ ሚሊሻ በአማራ ክልል የሚገኙ ቁልፍ ከተሞችን በቁጥጥራቸው ስር አዋሉ፡፡ ነገር ግን የመከላከያ ሰራዊቱ እነዚህን ከተሞች ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መልሶ ተቆጣጠሯል። በክልሉ የኢንተርኔት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በመዘጋቱ፣ ሌሎች የመረጃ መለዋወጫ መንገዶች በከፊል በመቋረጣቸው፣ የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመናገር እና በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ባሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ እና የበቀል እርምጃን ፍራቻ የተነሳ በአማራ ክልል የተከሰተው ግጭት በሰብዓዊ መብቶች ላይ እያደረሰ ስላለው ተፅዕኖ የሚያሳዩ መረጃዎችን

“ከኛ ጋር ሳይሆን ሊፋለሟቸው ከመጡት አካላት ጋር ብቻ የሚዋጉ መስሎን ነበር። ”

በባህር ዳር ከተማ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወታደሮች ከህግ አግባብ ውጪ የተፈፀሙ ግድያዎች

*ማግኘት አስቸጋሪ የነበረ ሲሆን  ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በክልሉ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎቸ ቀስ በቀስ መውጣት ጀምረዋል፡፡ በክልሉ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ገጽታ በስፋት ለመረዳት ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በአማራ ክልል እየተካሄደ ባለው ገጭት ዙሪያ ያዘጋጀው ይህ የመጀመሪያ አጭር የምርመራ ሪፖርት የመከላከያ ሰራዊት ወታደሮች በአማራ ክልል መዲና በሆነችው  ባህር ዳር  ከተማ  ቢያንስ 11 ሰላማዊ ሰዎችን እና አንድ ሰላማዊ የሆነ  ወይም  በግጭት መሳተፍ ያቆመን (hors de combat[1]) ሰው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት (IHL) ህግጋትን በጣሰ መልኩ እንደገደሉ ሰንዷል። በዚህ አጭር ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት ከህግ አግባብ ውጭ የተፈጸሙ ግድያዎች በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ወንጀል ተብለው ሊፈረጁ የሚችሉ ናቸው።*

*ሪፖርቱ ነሀሴ 2 ቀን 2015 ዓ.ም. የመከላከያ ሰራዊቱ ወታደሮች ቀበሌ 14 ውስጥ በአቡነ ሃራ እና ልደታ አካባቢዎች ስድስት ሰላማዊ ሰዎችን ከህግ አግባብ ውጪ እንዴት እንደገደሉ ሰንዷል። መስከረም 29 እና 30 2016 ዓ.ም. የመከላከያ ሰራዊቱ አባላት ሰባ ታሚት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ቢያንስ አምስት ሰላማዊ ሰዎችን እና አንድ ሰላማዊ የሆነ ወይም በፍልሚያ መሳተፍ ያቆምን ሰውን ጨምሮ በአጠቃላይ ስድስት ሰዎችን ከህግ አግባብ ውጪ ገድለዋል።*

*አምነስቲ ኢንተርናሽናል በዚህ አጭር ሪፖርት ያቀረባቸውን ግኝቶች ምርምራ በዋናነት ያካሄደው ከጥቅምት 21 እስከ ታህሳስ 8 2016 ዓ.ም ባሉት ቀናት ሲሆን ታህሳስ 27 ቀን አንድ ተጨማሪ ቃለ መጠይቅ አድርጓል።  ለጥናቱ የሚረዱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በአማርኛ ቋንቋ ከተካሄዱ 32 የስልክ ቃለ መጠይቆች ነው፡፡ ቃለ መጠይቆቹም የተካሄዱት ከአይን እማኞች፣ ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከጤና ባለሙያዎች እና ከማህበረሰብ እና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ነው። በሪፖርቱ ከዚህ በተለየ መልኩ በግልፅ ካልተጠቀሰ በስተቀር በምርመራው  የተሳተፉ ግለሰቦች ስም እና ሌሎች ማንነታቸውን ሊገልጹ የሚችሉ ዝርዝር መረጃዎች በሪፖርቱ ውስጥ እንዳይካተቱ ተደርጓል፡፡ ይህንን ማድረግ ያስፈለገው በምርምራው ተሳታፊዎች ላይ በባለሥልጣናት ሊፈፀሙ የሚችሉ የበቀል እርምጃዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።*

*የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የቀውስ ማስረጃዎች ላብራቶሪ (Crisis Evidence Lab) የሳተላይት ምስሎችን፣ ፎቶግራፎችን እና የቪዲዮ ማስረጃዎችን በመተንተን በግድያዎቹ ዙሪያ ዐውዳዊ መረጃዎችም አጠናክሯል።*

*የካቲት 1 ቀን 2016 ዓ.ም. አምነስቲ ኢንተርናሽናል የጥናቱን ቅድመ ግኝቶች ለፍትህ ሚኒስቴር እንዲሁም በግልባጭ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አጋርቷል። ይሁን እንጂ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከእነዚህ አካላት ምንም ምላሽ አላገኘም።*

*በፋኖ ሚሊሻ እና በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት መካከል እየተደረገ ያለው ግጭት በመጀመሪያ የተቀሰቀሰው ሐምሌ 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በባህር ዳር ከተማ አቡነ ሃራ ተብሎ በሚታወቅ አካካባቢ በሚገኘው ሙሉጌታ ሪል ስቴት ሰፈር ነው።  የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገለፁት የፋኖ ሚሊሻ አመራር የሆኑት አቶ ዘመነ ካሴ በዚህ ሪል ስቴት ውስጥ በሚገኝ አፓርትመንት ነዋሪ ነበሩ።  ሐምሌ 29 ቀን ጀምሮ የፋኖ ሚሊሻ በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ በርካታ ሰፈሮችን የተቆጣጣሩ ሲሆን ሚሊሻ ከተቆጣጠሯቸው ስፍራዎች ውስጥ አባይ ማዶ እየተባለ የሚጠራው ቀበሌ 11፣  ቀበሌ 14፣ 16፣ 13፣ 7፣ እና 8 ይገኙባታል   ነሐሴ 3 ቀን 2023 ዓ.ም. የፋኖ ሚሊሻ ተቆጣጥረዋቸው የነበሩትን እነዚህን አካባቢዎች ለቀው ወጡ።  ነሀሴ 5 እና 6 በአቡነ ሃራ እና ልደታ ተብልው በሚታውቁት አካባቢዎች ስድስት ሰላማዊ ሰዎች በመከላከያ ሰራዊት ወታደሮች ከህግ አግባብ ውጭ መገደላቸውን አምነስቲ ኢንተርናሽናል አረጋግጧል።*

*ግጭቱ በባህር ዳር ከተማ ከተቀሰቀሰ ከሁለት ወራት በኋላ መስከረም 29 2016 ዓ.ም በሌሎች የከተማው ክፍሎች በተለይም በሰባ ታሚት አካባቢ  እንደገና አገረሸ። በዚህ አካባቢም አምስት ንፁሃን ዜጎች እና ጤና ጣቢያ ውስጥ ህክምና እየተከታተለ የነበረ አንድ ታካሚ ከህግ አግባብ ውጪ  በመከላከያ ሰራዊት ወታደሮች መገደላቸውን አምነስቲ ኢንተርናሽናል አረጋግጧል። መስከረም 29 እና 30 2016 ዓ.ም. የመከላከያ ሰራዊት ወታደሮች እዚሁ ጤና ጣቢያ ውስጥ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎችን ደብድበዋል፤ በጠበንጃም አስፈራርተዋል። በዚህ አካባቢ የግድያ ሰለባ ከሆኑት መካከል ሦስቱ የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ወንድማማቾች ናቸው።*

*በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ (IHL) መሰረት በህመም ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ከግጭት ውጭ የሆኑ  (hors de combat)" ታጣቂዎችን ጨምሮ በግጭት ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸውን ሰዎችን መግደል  የጦር ወንጀል ነው። ከህግ አግባብ ውጭ የሚፈጸሙ ግድያዎች የሰዎችን  በህይውት የመኖር መብትን በዘፈቀደ ስለሚነፍጉ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግንም  ይፃረራሉ።*

*አምነስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት እንዲያቆም እና የኢትዮጵያ መንግስትም በእነዚህ ጥቃቶች  ላይ ምርመራ በማድረግ  ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ እንዲያቀርቡ  ይጠይቃል። በኢትዮጵያ የህግ ተጠያቂነት አለመኖር  ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን የሚፈጽሙ አካላትን የሚያደፋፍር እና  ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው። በዚህ ሪፖርት የተካተቱትን እና በትግራይ ተቀስቅሶ ወደ አፋር እና አማራ ክልል በተካሄደው የትጥቅ ግጭት አውድ ውስጥ  የተፈፀሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በአምነስቲ ኢንተርናሽናል በቀረቡ ምርመራ ሪፖርቶች የተዘገቡ ወንጀሎችን የፈፀሙ አካላትን ተጠያቂ ሊያረግ የሚችል ታዓማኒነት ያለው የፍትህ እና ተጠያቂነት አሰራር እስካልተዘረጋ ድረስ ሰላማዊ ዜጎች የጥቃት ሰለባ እንደሆኑ ይቀጥላሉ፤ የጤና እና ትምህርትን ጨምሮ ሌሎች  መብቶቻቸውም  በግጭቶች የተነሳ አደጋ ላይ ይወድቃሉ።*

---

[1] "ሆር ደ ኮምባ" የተሰኘው የፈረንሣይኛ ቃል በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ መሰረት የቆሰለ ወይም የታመመ ተዋጊን ለማመልከት የሚያገለግል ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች በግጭት መሳተፍ እንደማይችሉ ተደርገው የሚቆጥሩ ሲሆን በዚህም ምክንያት ከጥቃት ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

# ማጠቃለያዎች እና ምክረ-ሀሳቦች

በአማራ ክልል እየተፈፀሙ ካሉት የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ (IHL) እና የሰብዓዊ መብት ህግጋት ጥሰቶች አንፃር በዚህ አጭር ሪፖርት የቀረቡት  በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወታደሮች በባህር ዳር ከተማ ሰላማዊ ዜጎችን ሲገድሉ እና አንዳንዴም የቤተሰብ አባላት ወዳጅ ዘመዶቻቸውን እንዳይቀብሩ ሲከለክሉ ታይቷል። በአንድ አጋጣሚ አንድ አስከሬን ሌሊቱን ሙሉ ጎዳና ላይ ተጥሎ አድሯል።  የቤተሰቡ አባላትም  በኢትዮጵያ ትልቅ ትርጉም የሚሰጠውን የቀብር ሥነ ሥርዓት በአግባቡ  የመፈፀም እድል ተነፍገው ለበለጠ ሰቆቃ ተዳርገዋል። በዚህ ሪፖርት እንደተገለጸው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወታደሮች የ14 ዓመት ወንድ ልጅን  እና ጤና ጣቢያ ውስጥ ህክምና እየተደረገለት የነበረ የ20 ዓመት ወጣትን ረሸነዋል።

ከታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በሰሜን ኢትዮጵያ ከተከሰተውን የትጥቅ ግጭት ጋር በተገናኘ የጦር ወንጀሎች እና በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሊሆኑ የሚችሉ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ (IHL) እና የሰብአዊ መብቶች ህግጋት ጥሰቶችን   በስፋት ዘገቧል። ድርጅቱ የኢትዮጵያ እና የኤርትራ መንግሰታት እንዲሁም የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ አጋሮች ለፍትህ እና ተጠያቂነት ቅድሚያ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ አሳስቧል ።

በትግራይ ክልል ውስጥ የተጀመረው ግጭት ካበቃ ከአንድ አመት በኋላ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሌላ የትጥቅ ግጭት (በአማራ ክልል) የጦር ወንጀል መፈጸሙን ቀጥሏል።

ወንጀል ፈፃሚዎችን ለፍርድ አለማቅረብ በቀጣይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዲፈፀሙ እና በሰላማዊ ዜጎች ላይ ለሚደርሱ በደልና ሰቆቃዎች አይነተኛ መንስኤዎች መሆናቸውን አፅንዖት በመስጠት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በኢትዮጵያ ፍትህ እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት**

- ለገለልተኛ ሚዲያ ተቋማት እንዲሁም ለአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በክልሉ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እንዲከታተሉ ያልተገደበ ፍቃድ እንዲሰጥ፤
- በአማራ ክልል ላይ የተጣለውን የኢንተርኔት እገዳ እና በአንዳንድ የክልሉ ዞኖች የሚታየውን የግንኙነት መቋረጥ እንዲያነሳ፤
- ከታህሳስ ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እና በአጋሮቹ የዓለም አቀፍ ህግን በተፃረረ መልኩ የተፈፀሙ ወንጀሎችን አጣርቶ በፍርድ ቤት ክስ እንዲመሰረትባቸው እንዲያደርግ፤ እና
- በተባበሩት መንግስታት  *ከፍርድ ውጭ፣ በዘፈቀደ እና በጅምላ የሚፈፀሙ ግድያዎች  ልዩ ራፖርተር* በአማራ ክልል    ውስጥ እየተደረገ ካለው ግጭት ጋር በተያያዘ በባህር ዳር ከተማ ከህግ አግባብ ውጪ ተፈፅመዋል የተባሉ የግድያ ወንጀሎችን እና በአጠቃላይ በክልሉ በተፈፀሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ምርመራ እንዲያደርጉ በተቻለ ፍጥነት ግብዣ እንዲያቀርብላቸውአምንስቲ ያሳስባል ፡፡

**ለተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት (HRC) አባል ሀገራት**

- ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ የሚያደርገውን ክትትል እንደገና እንዲጀምር እና የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን (ICHREE) ምርመራ ግኝቶችን ለመከታተል የሚያስችለውን አሰራር ለመዘርጋት አፋጣኝ እርምጃዎችን እንዲወስድ አምንስቲ ያሳስባል ።

**ለአፍሪካ አንድነት የሰላምና ፀጥታ ምክር ቤት**

- ጉዳዮን በአጀንዳነት ለውይይት ማቅረብን ጨምሮ በክልሉ ሰላለው ግጭት ሚያከናውናቸውን ይፋዊና ይፋዊ ያልሆኑ ጥረቶችን እንዲያጠናክር፤ እና
- *በአፍሪካ በሞት ቅጣት እና ከፍርድ ውጭ፣ በዘፈቀደ ወይም በጅምላ በሚፈፀሙ ግድያዎች እና በግዳጅ በሚሰወሩ ሰዎች ዙሪያ የሚሰራው የአፍሪካ ኮሚሽን የስራ ቡድን* በባህር ዳር ከተማ  ከህግ አግባብ ውጭ ተፈፀሙ የተባሉ ግድያዎችን መርምሮ  ግኝቶቹን እና ምክረ ሃሳቦቹን ለምክር ቤቱ እንዲያቀርብ ጥሪ እንዲያደርግ አምንስቲ ያሳስባል።

**ለኢትዮጵያ የልማት አጋሮች**

- ጥቃቶችን ለማስቆም ከሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ አጋሮቻቸው ጋር አብረው እንዲሰሩ፣
- *የተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት*  በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ላይ የሚያደርግውን ክትትል በድጋሚ እንዲጀምር ግፊት ከማድረግ በተጨማሪ  የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን  (ICHREE) የመጨረሻ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱ ምክረ ሀሳቦችን ተፈፃሚነት አስመልክቶ ክትትል እንዲያደርጉ፣
- የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን ማማከር እና መደገፍ እንዲሁም |መንግስት በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ወሳኝ ሚና ያላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና ሚዲያዎች ላይ የሚደርሰውን ወከባ እንዲያቆም  ወትውታ እንዲያደርጉ አምንስቲ ያሳስባል ።

## Contact

**info@amnesty.org**

**amnesty.org**

facebook.com/
**AmnestyGlobal**

**@Amnesty**

Amnesty International
Peter Benenson House
1 Easton Street
London WC1X 0DW, UK



በሌላ ቦታ ካልተጠቀሰ በስተቀር  በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው ይዘት በክሪኤቲቭ ኮመንስ(Creative Commons) (መለያነት ፣ ለንግድ ያልሆነ ፣ ምንም ተዋጽኦዎች ፣ በአለምአቀፍ 4.0) ፈቃድ ተሰጥቶታል። ይህንን ሊንክ ይመልከቱ
creativecommons.org/licenses/by-nc-nd/4.0/legalcode

የቅጂ መብት ባለቤቱ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባለሆነበት ሁኔታ ይህ ጽሁፍ
ለክሪኤቲቭ ኮመንስ ፈቃድ ተገዥ አይሆንም፡፡

ለበለጠ መረጃ፥ የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን የፈቃድ ገፅ የመልከቱ



**መረጃ ጠቋሚ፤AFR 25/4569/2021**

ህትመት የካቲት2016 ዓ.ም.

**ሪፖርቱ በመጀመሪያ የቀረበበት ቋንቋ፤ እንግሊዝኛ**



© አምነስቲ ኢንተርናሽናል 2016 ዓ.ም.